

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

# የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የ2025 ዓመታዊ ሪፖርት

ማርች ፤ 2025

## የይዘት ሰንጠረዥ (Table of Contents)

ሀ - የመንፈሳዊ አገለግሎት ዓመታዊ ሪፖርት ገጽ 2

ለ - የሰንበት ትምህርት ቤት ዓመታዊ ሪፖርት ገጽ 2

ሐ - በጽሕፈት ቤት የተከናወኑ ዋና ዋና ጉዳዮች ገጽ 3

መ - የጥገና እና እድሳት ዓመታዊ ሪፖርት ገጽ 4

ሠ - የዕቅድና ልማት (የፋይናንስ) ዓመታዊ ሪፖርት ገጽ 5

## <u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ</u>

የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የ2025 ዓመታዊ ሪፖርት

### <u>ሀ - የመንፈሳዊ አገለግሎት ዓመታዊ ሪፖርት</u>

፩ - በቤተ ክርስቲያናችን ከሰኞ እስከ ዓርብ የሠርክ ጸሎትና በቀጠሮ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል።

፪ - በየሳምንቱ ቅዳሜ ጧት ጸሎተ ኪዳን ተደርሷል በቀጠሮ የምክር አገልግሎትም ተሰጥቷል።

፫ - በየሳምንቱ ቅዳሜ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለልጆች ተሰጥቷል።

፬ - ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በየሳምንቱ ቅዳሜ የአማርኛ ቋንቋ ተምረው ማንበብና መጻፍ ችለዋል።

፭ - የሃይማኖት ትምህርት ተምረዋል።

፮ - ሳምንታዊ የእሁድ አገልግሎት ከሌሊቱ 4:00am ጀምሮ ጸሎተ ነግህ ኪዳንና ቅዳሴ ተሰጥቷል ።

፯ - ጸሎተ ፍትሐት ተደርጓል።

፰ - በየሳምንቱ እሁድ የስብከተ ወንጌል በዙም በተለያዩ መምህራን ትምርት ተሰጥቷል።

፱ - የታህሣሥ አማኑኤል እና የግንቦት አማኑኤል በዓለ ንግሥ የየካቲትና የነሐሴ 16 ኪዳነ ምሕረት በዓለ ንግሥ ከተለያየ ስቴት በመጡ ካህናት ሊቃውንት ዲያቆናት እና ምእመናን በታላቅ ድምቀት ተከብሯል።

፲ - ዲያቆናት ቅዳሜ ትምህርት ተምረዋል።

፲፩ - እናቶች ቅዳሜ ቅዳሜ የቅዳሴ ተሰጥዎ ትምህርት ተምረዋል።

## ለ - የሰንበት ትምህርት ቤት ዓመታዊ ሪፖርት

የደብራችን የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ባሳለፍነው 2025 ዓ.ም የአገልግሎት ዘመን የተለያዩ ተግባሮችን አከናውኗል።

፩ - በዕለተ ሰንበት ተገኝተው ያጠኑትን እና ያዘጋጁትን መዝሙሮችን አቅርበዋል።

፪ - በካህናት አባቶች ትዕዛዝ ሲጠየቁ የተለያዩ አገልግሎቶችን እገዛ አድርገዋል።

፫ - በዓመታዊ እና ዓበይት በዓላት ተገኝተው ከዝማሬ በተጨማሪ ከምእመናን ጋር በመተባበር የፅዳትና የተለያዩ አገልግሎቶችን አከናውነዋል።

፬ - ሕፃናቶችን መዝሙር በማስጠናትና በማሰልጠን አስተባብረዋል።

፭- ከቤ/ክ ምእመናን በፈቃደኝነት ተውጣተው ሕፃናትን በማስተማር ከሚያገለግሉ መምህራን ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ሁሉ አገልግሎት አከናውነዋል።

## ሐ - በጽሕፈት ቤት የተከናወኑ ዋና ዋና ጉዳዮች

፩ - ማርች 30 ፤ 2025 ሰበካ ጉባኤ የጠቅላላ ስብሰባ ጠርቶ የ2024 ዓ/ም ሪፖርት አቅርቧል።

፪ - የ2025 በጀት ተዘጋጅቶ ለምእመናን ቀርቦ ጸድቋል።

፫ - በዓላትን በአግባቡ እንድናከብር ሰበካ ጉባኤ አስተባብሯል ፤ በዓላቱም የኪዳነ ምሕረት እና የአማኑኤል በዓለ ንግስ ፤ የመስቀል በዓል ፤ ሲሆኑ በተጨማሪም ዘጠኙንም ዓበይት በዓላትን ፤ ትስብዕት ልደት ፤ ጥምቀት ፤ ደብረ ታቦር ፤ ሆሣዕና ፤ ስቅለት ፤ ትንሣኤ ፤ ዕርገት እና ጰራቅሊጦስ ተከብረዋል።

፬ - ሰበካ ጉባኤው ለቤተ ክርስቲያናችን ገንዘብ የማግኛ መንገድ አቀነባብሮ የሚከተሉት የገንዘብ አሰባሰብ (Fund Raising) ተደርጓል:

- የአዲስ ዓመት በዓል (ዕንቁጣጣሽን) በማክበር ትኬት ተሸጦ ገንዘብ ስብሰባ ተደርጓል
- የኢትዮጵያን ቀን ፕሮግራም ላይ ተሳትፈናል ፤ በፕሮግራሙ ላይ ቁሳቁሶችን በመሸጥ ገንዘብ ተሰብስቧል
- ጊቪንግ ቱዩስዴ (Giving Tuesday) በሚባለው የገንዘብ አሰባሰብ ዓመታዊ ፕሮግራም ላይ ተሳትፈን ገንዘብ አግኝተናል

፭ - መተዳደሪያ ደንቡን በመከተል በ2025 ሁለት ቤተሰብ አባል አድርገን መዝግበናል።

፮ - ለበዓለ ንግሥ ወይም ክብረ በዓል ለማክበር የመጡ ካህናትን አስተናግዷል።

፯ - ምእመናን የሚያበረክቱትን ገንዘብ በዓመቱ መጨረሻ ለታክስ እንዲጠቅማቸው ደብዳቤ አዘጋጅቶ ሰጥቷል።

፰ - የሰበካ ጉባኤው በየጊዜው እየተሰበሰበና እየተወያየ ለቤተ ክርስቲያኑ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ እየተከታተለ አስፈጽሟል ፤ በተለይም በኢንሹራንስ ጥያቄ መሠረት ጥገናዎች በወቅቱ እንዲፈጸሙ አድርጓል።

፱ - በኦዲተራችን በተሰጠን መመሪያ መሠረት የገንዘብ አወጣጥ ቅጽ አዘጋጅቶ በስራ አውሎታል።

## <u>መ - የጥገና እና ዕድሳት ዓመታዊ ሪፖርት</u>

ለቤተ ክርስቲያናችን ሕንፃ አስፈላጊውን እድሳትና ጥገና በማድርግ ባሳለፍነው ዓመት የሚከተሉትን ተግባሮች አከናውኗል።

፩ - በ January 16, 2025 :- የአፓርትመንቱን ቺሚኒ እንዲፀዳ ተደርጓል።

፪ - በ January 18, 2025 ፦ በአደራሹ መድረክ ላይ ሁለት መብራቶች ተቀይረዋል እንዲሁም ስምንት ሶኬቶች/አውትሌቶች ተቀይረዋል ።

፫ - በ February 22, 2025 :- የቤተ ክርስቲያታችን ሎጎ መብራት ተቀይሮለት እንደሰራ ተደርጓል ።

፬ - በ July 6, 2025 :- ሦስት አዳዲስ በሮች ተገዝተዉ ሁለቱ በአፓርትመንት በኩል :- ለንዋየ ቅድስት ክፍል እና በኪችን በኩል ያለውን በር እንዲሁም በአደራሹ በሞርትን በኩል ያለውን በር በአዲስ ተቀይረዋል።

፭ - በ July 16, 2025 አዲስ የሣር መቁርጫ ማሽን ተገዝቷል ።

፮ - በ September 7, 2025 ለቤተ መቅደስ ውስጥ አዲስ የማቀዝቀዣ ኤሲ ቬንት ተገጥሞ ተሰርቷል ።

፯ - በ September 10, 2025 :- በባክ ያርድ በኩል ያለውን የእንጨት ድልድይ አፍርሶ ቆሻሻውን ወሶዶ ጥሎ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ሲል ኮቲንግ በማድረግ እድሳት ተደርጎለታል።

፰ - በ November 28, 2025 :- በዬል አቬኒዩ በኩል ያለው፣ የተበላሸውን የእግረኛ መሄጃ በኮንክሪት ጥገና ተደርጓል።

፱ - በ November 3, 2025 :- በ Lifeway Mobility Company አዲስ ድልድይ (Ramp) ተሰርቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል ።

፲ - በ December 24, 2025 የቤተ ክርስቲያን ቤዝመንት የልጆች መማሪያ ክፍሎችን እና መፀዳጃ ክፍሎችን ኮርኒስ እና መብራቶች በአዲስ ተቀይረው እንዲሰሩ ተደርጓል ።

፲፩ - በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን በበጎ ፈቃደኝነት የተለያዩ በውስጥም በውጭም ያለዉን የፅዳት ሥራዎችን ሣር ማጨድ ፣ እስኖ መጥረግ ፣ ቆሻሻ በማጽዳት ትብብር አድርገዋል።

## <u>ሠ - የዕቅድና ልማት (የፋይናንስ) ዓመታዊ ሪፖርት</u>

፩ - በ2025 ገንዘብ ማሰባሰብ የተደረገው በአራት (4) መንገዶች በኩል ነው። እነዚህም፦

- በፊላደልፊያና እና አካባቢው በተደረገው የኢትዮጵያ ቀን (Ethiopian’s Day)
- የኢትዮጵያን ዓዲስ ዓመት በዓል አስመልክቶ
- በ ጊቪንግ ቲውስዴይ (Giving Tuesday) እና
- በንዋየ ቅድሳት ሽያጭ

፪ - በ9/6/25 የኢትዮጵያ ቀን አስተባባሪ ኮሚቴ (Ethiopian's Day Planning Committe) ባዘጋጀው በዓል ላይ ቤተ ክርስቲያናችን ተሳትፎ አድርጎ በዕለቱ ከልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ሽያጭ $2,555 ለቤተ ክርስቲያናችን ገቢ ሆኗል።

፫ - በ9/13/25 ለቤተ ክርስቲያናችን ገቢ ማሰባሰቢያ የPicnic ዝግጅት ተደርጓል። እንደምታስታውሱት፣ በሁላችሁም ትብብር ዝግጅታችን በአማረ ሁኔታ ካሰብነው በላይ ውጤታማ ሆኖልናል። በዚህ ዝግጅት $3,582 ለቤተ ክርስቲያን ገብቷል።

፬ - በአቶ ኤፍሬም ካባ አደራጅነት በጊቪንግ ቲውስዴይ (Giving Tuesday) የቤተ ክርስቲያናችንን ቤዝመንት የልጆች መማርያ ክፍሎች ኮርኒስ እና መብራት እንዲታደስ በተወሰነው መሰረት $5,430 ገቢ ተደርጓል።

፭ - የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ለንዋይ ቅድሳት ሽያጭ እንዲቀርብ አበርክተዋል። በ2025 ከንዋይ ቅድሳት ሽያጭ $8,231 ገቢ ሆኗል።

በአጠቃላይ በ 2025 በእቅድና ልማት ክፍል በኩል $19,798 ለቤተ ክርስቲያናችን ገቢ ማድረጉን ሲገልጽ በታላቅ አክብሮት ሲሆን እንዲሁም በቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን እግዚአብሄር ይስጥልን በማለት ምስጋና ያቀርባል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት
ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ